# አንዲስዋ የእግር ኳስ ኮከቧ

Eden Daniels

Eden Daniels

Dawit Girma

2

አማርኛ am

አንዲስዋ ወንዶች ልጆች ኳስ ሲጫወቱ እየተመለከተች ነው። ከልጆቹ ጋር ተቀላቅላ መጫወት ፈለገች። አሰልጣኙንም ከልጆቹ ጋር እግር ኳስ ልምምድ መስራት ትችል እንደሆነ ጠየቀችው።

አሰልጣኙ እጆቹን ወገቡ ላይ አደረገ። ‹‹በዚህ ት/ቤት ወንድ ልጆች ብቻ ናቸው እንዲጫወቱ የተፈቀደላቸው፣›› አለ።

ልጆቹ ሄዳ ‹‹ኔት ቦል›› እንድትጫወት ነገሯት። እነሱም ለሴት ‹‹ኔት ቦል›› እንደሆነ፣ እግር ኳስ ግን ለወንድ ልጆች እንደሆነ ነገሯት። አንዲስዋ ተናደደች።

በሚቀጥለው ቀን ት/ቤቱ ታላቅ የአግር ኳስ ግጥሚያ ነበረበት። አሰልጣኙ በጣም ተጨንቋል፤። ምክንያቱም የቡድኑ ወሳኝ ተጫዋች በህመም ምክንያት መጫወት ባለመቻሉ ነበር።

አንዲስዋ ወደ አሰልጣኙ እየሮጠች ሄዳ እንድትጫወት እንዲፈቅድላት ለመነችው። አሰልጣኙ ምን ማድረግ እንዳለበት ግራ ገባው። ከዚያም አንዲስዋ ቡድኑን እንድትቀላቀል ፈቀደላት።

ጨዋታው በጣም ፈታኝ ነበር። በመጀመሪያው ግማሽ
የጨዋታው ክፍለ ጊዜ ማንም ጎል ሊያስቆጥር አልቻለም።

በሁለተኛው አጋማሽ የጨዋታው ጊዜ፤ ከልጆቹ መካከል አንዱ ኳስ ለአንዲስዋ አቀበላት። ኳሱን በፍጥነት ወደ ጎል እያንከባለለች ሄደች። ከዚያም ኳሱን በኃይል አክርራ መታችውና ጎል አስቆተረች።

ተመልካቹ በደስታ አበደ። ከዚያ ቀን ጀምሮ ሴቶችም በት/ቤቱ ኳስ እንዲጫወቱ ተፈቀደላቸው።

# Global Storybooks

globalstorybooks.net

## አንዲስዋ የእግር ኳስ ኮከቧ

Eden Daniels
Eden Daniels
Dawit Girma

CC BY NC